

# በትምህርት ቤቶች የሚፈፀም ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል የወጣ ረቂቅ መመሪያ

ትምህርት ሚኒስቴር
2006

# Code of Conduct on Prevention of School Related Gender Based Violence in Schools

Ministry of Education

2014

# በትምህርት ቤቶች የሚፈፀም ጾታዊ ጥቃትን ከመከላከል የወጣ ረቂቅ መመሪያ

# Code of Conduct on Prevention of School Related Gender Based Violence in Schools

ትምህርት ሚኒስቴር

2006

Ministry of Education

2014

# መግቢያ

በኢፌዴሪ ህገ መንግስትና በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችና ድንጋጌዎች የተረጋገጡትን የሰው ልጆች እኩልነት ክብርና ነፃነት በየትኛውም ቦታና ጊዜ ማክበርና ማስከበር ግዴታ በመሆኑና ማንኛውም ህጻን በነፃነት የመማር ፤ መልካምና ምቹ የመማሪያ አካባቢ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ ፤

ጾታዊ ጥቃት የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲሆን በተለይም በትምህርት ቤቶች አካባቢ እየተፈፀመ ያለው የጾታዊ ጥቃት ተግባር ጤናማ የትምህርት ሂደት እንዳይኖር እንቅፋት እየሆነ በመምጣቱ ፤

የጾታዊ ጥቃት በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚፈፀም ተግባር ቢሆንም ፣ በተለይ የችግሩ ተጋላጭ የሆኑት ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከወንዶች እኩል በመከታተል ውጤታማ እንዳይሆኑና እንዲሁም የሴት ተማሪዎቹ የትምህርት ተሳትፎ ብቃትና ውጤታማነት የሚያቀጭጭ በመሆኑ ፣

በቅድመ መደበኛ ፣ በአንደኛ (1-8)ና ሁለተኛ ደረጃ (9-12) በሚገኙ ትምህርት ቤቶች


# Preamble

WHEREAS it is mandatory to respect rights of equality, dignity and freedom of humanity according to the constitution of FDRE, International Human Rights Agreements and declarations, all children have the right to learn freely within friendly and conducive learning environment;

WHEREAS gender based violence is also violence of human rights. Gender based violence that is happening around schools is becoming a great obstacle against healthy and smooth teaching learning process;

WHEREAS both women and men are victims of school related gender based violence, females are more vulnerable. This makes it difficult for girls to attend their schooling at equal footing with boys and hence hinders their attendance, academic performance and efficiency;

WHEREAS it is crucial to create a teaching-learning environment that is free from gender based



# ክፍል አንድ፡ - ጠቕላላ Part One: General

እየተፈፀሙ ያሉ የጾታዊ ጥቃት ተግባራትን ለመከላከል ፣ ለመቀነስና ብሎም በሂደት ለማጥፋት ከጾታዊ ጥቃት የጸዳ ምቹ አካባቢ በዘላቂነት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

የትምህርት ሚኒስቴር የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል ፡፡

violence; to prevent, minimize and eventually eliminate acts of gender based violence at pre-school, primary school (1st to 8th grades) as well as secondary school (9th to 12th grades) levels.

This code of conduct is issued by the Federal Ministry of Education with its mandate given to it by Proclamation number 691/2010, to regulate the power and responsibility of its executive bodies.

# ክፍል አንድ፡ - ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “በትምህርት ቤቶች የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃትን በሚመለከት የወጣ መመሪያ” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ፤

2.1.“ፆታዊ ጥቃት” ማለት አንድን ግለሰብ ሴት ወይም ወንድ በመሆኑ ማለትም ፆታን ወይም ስርዓተ ጾታን መሠረት በማድረግ በግለሰቡ ስነ ልባዊና አካላዊ ጤንነት ፤ እድገት እና ማንነት ላይ አሉታዊ ጉዳት የሚያደርሱ ማንኛዉንም ተግባራት መፈጸም ሆኖ ጥቃቱም ወሲባዊ ፤ አካላዊ ፤ ስነልቦናዊ እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃትን ያካትታል ፡፡

2.1.1 “ወሲባዊ ጥቃት” ማለት ወሲባዊ ትንኮሳ ፤ወሲባዊ ብዝበዛ ፤ መድፈር ሰዎችን ያለፍላጎት ለወሲብ ንግድ እንዲሰማሩ ማድረግን ያካትታል

# Part One: General

## 1. Shorter Title

This regulation can be referred to as “Code of Conduct on Prevention of School Related Gender Based Violence in Schools, shortly SRGBV.”

## 2. Definitions

Unless and otherwise the terminologies implied another definition, under this regulation:

2.1. “Gender Based Violence”: includes any form of sexual, physical, psychological, social as well as economical violence based on sex or gender that results in harming psychological, physical wellbeing and, growth and personality of an individual.

2.1.1. “Sexual Violence”: includes sexual harassment, sexual exploitation, rape, trafficking/ forcing for commercial sex work.

**2.1.2**”አካላዊ ጥቃት” ማለት ፆታን መሰረት በማደረግ መደብደብ ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈጸም አካላዊ ቅጣት ፣ ቅሚያና የጉልበት ብዝበዛን ያካትታል

**2.1. 3**”ስነልቦናዊ ጥቃት” ማለት ፆታን መሰረት አድርጎ የሚፈፀም ዘለፋ ፣ የቅጽል ስም መስጠት ፣ ማስፈራራት ፣ ማንቋሸሸና የስነልቦና ጫና ማሳደርን ያካትታል

**2.1.4**” ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃት” ማለት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችንና ጥቅሞችን ጾታን መሰረት በማድረግ እንዳያገኙ መከልከልን ያካትታል ፡፡

**2.2.** “የትምህርት ቤት ማህበረሰብ” ማለት በቅድመ መደበኛ ፣በአንደኛ (1-8) ና ሁለተኛ ደረጃ (9-12) ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የሚገኙ መደበኛና የማታ ተማሪዎች ፣ መምህራን ፣ርእሰ መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ያጠቃልላል ፡፡

**2.3.** “ርእሰ መምህር” ማለት አንድን ትምህርት ቤት በበላይነት እንዲመራ የተመደበ ሃላፊ ሆኖ

**2.1.2.** “Physical Violence”: includes gender based beating, physical punishment at school, robbery, labor exploitation.

**2.1.3.** ''Psychological Violence”: includes gender based harassment, name-calling, threatening, bullying, negative psychological influence.

**2.1.4.** “Social and Economic Violence”: gender based denial of social and economic services as well as benefits.

**2.2.** “School Society”: includes regular and extension students, teachers, principals and support staff in pre-school, primary school ($1^{st}$ to $8^{th}$ grades) as well as secondary school ($9^{th}$ to $12^{th}$ grades).

**2.3.** “Principals”: one who is entrusted to manage a school which also includes the vice

ምክትል ርእሳነ መምህራንን ያካታል ፡፡

2.4. "አስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ" ማለት የአስተዳደር ፣የቢዝነስ አመራር ፣ የፋይናንስና ሂሳብ ስራ ፣ጥገናና ጥበቃ የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያከናዉን የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ

2.5"መምህር" ማለት በትምህርት ቤቱ በመደበኛ ፣ መደበኛ ባልሆነና በማታ ትምህርት በማስተማር ወይም በማመቻቸት ተግባር ላይ የተሰማራ ግለሰብ ነዉ

2.6" ተማሪ" ማለት በትምህርት ቤቱ በመደበኛ ፣ መደበኛ ባልሆነና በማታ ትምህርት በመማር ተግባር ላይ የተሰማራን ያካትታል

2.7."ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (ወተመህ)" ማለት በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በወላጆችና በትምህርት ቤቱ መካካል ያለዉን ጤናማ ግንኙነትና ምቹ የመማር ማሰተማር ሂደት ለመፍጠር የተመሰረተ ህብረት ነዉ።

2.8. "ትምህርት ቢሮ" ማለት የክልሉን ትምህርትና ስልጠና ለመምራት የተቋቋመ የክልል መ/ቤት ነው

principal

2.4. "Administration and Support staff": includes staff of a school that is engaged in administration, business management, Finance and Accounting, Maintenance, Security and other similar activities

2.5. "Teacher": a staff that is engaged in teaching or facilitating regular, part-time as well as extension class sessions.

2.6. "Student": includes a person who is attending formal, non-formal and/or extension class sessions.

2.7. "Parent Teacher Student Association": an association in a school that is established to create and follow-up healthy relationship and conducive teaching-learning environment amongst parents, students and teachers which is entrusted with the responsibilities as indicated in the school management guide line of the MoE

2.8. "Education Bureau": regional office that is established to guide and lead the academia (teaching and training) in a region

2.9. “ትምህርት ቤት” ማለት የቅድመ መደበኛ ፣የአንደኛ (1-8) ና የሁለተኛ ደረጃ (9-12) ትምህርትን በመስጠት ላይ የተሰማራ የመንግስት ፣የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ነው

2.10. “ክልላዊ መንግስት” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተገለጹትን የክልል መንግስታትን ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል።

2.11.” የፆታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ” ማለት በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የሚቋቋም የፆታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ነው ፡፡

2.12.”ተገቢ ጥበቃ” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት አቤቱታ ላቀረበ ፣ የጾታዊ ጥቃት አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ አባል ፣ምስክርነት ለሰጠ ፣እንዲሁም ዉሳኔ ለሰጠ የትምህርት ማህበረሰብ አባል አቤቱታ በማቅረቡ ፣ በሰጠዉ የምስክርነት ቃል ወይም ባቀረበዉ የዉሳኔ ሃሳብ ከሚደርስበት አሉታዊ ጫና ለመከላከል የሚደረግ ጥበቃ ነዉ።

2.13.”የዲሲፕሊን ኮሚቴ” ማለት የፌደራል የመንግስት ሰራተኞች

2.9. “School”: a private, governmental or non-governmental institution that provides education at pre-school, primary school (1st to 8th grades) as well as secondary school (9th to 12th grades) levels

2.10. “Regional Government”: regional governments that are listed in the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Article 47(1) including the federal city administrations of Addis Ababa and Dire Dawa.

2.11. “School Related Gender Based Violence Complaints Investigation and Decisions Recommending Committee”: a committee established by the school principal to hear complaints of gender based violence, clarify the complaints and provides decisions

2.12. “Legitimate Protection”: a protection from negative influences provided for those who make complaints of gender based violence, the members of Gender Based Violence Complaints investigation and Decisions Recommending Committee , those who testify to/against these cases, decision makers who conduct according to this regulation.

2.13. “Discipline Committee”:

የዲሲፕሊንና ቅሬታ አቀራረብና አፈጻጸም ደንብ ቁጥር 77/1994 መሰረት የተቋቋመ ኮሚቴ ነዉ።

2.14. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸዉ በሴትም ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

3.1. ይህ መመሪያ በቅድመ መደበኛ ፣ በአንደኛ (1-8) ና ሁለተኛ ደረጃ (9-12) ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የትምህርት ማህበረሰብ አባላት መካከል በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥም ሆነ ውጪ ጾታዊ ጥቃትን በሚፈጽሙት ላይ ተግባራዊ ይሆናል ፡፡

3.2. ይህ መመሪያ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በቅድመ መደበኛ ፣ በአንደኛ (1-8)ና ሁለተኛ ደረጃ (9-12) ትምህርት ቤቶች ላይ ተግባራዊ ይደረጋል።

3.3. በተራ ቁጥር 3.2 የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብና በማጣጣም የጾታዊ ጥቃት መመሪያ ማዉጣት ወይም ይህንን መመሪያ ሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ ፡፡

a committee established according to Federal Public Servants Complaints Reporting Execution regulation number 77/2011

## 3. Limit of Application

3.1. This code of conduct is applicable on whoever commits acts of school related gender based violence in pre-school, primary school (1st to 8th grades) as well as secondary school (9th to 12th grades) setting.

3.2. This code of conduct is also applicable in pre-schools, primary schools (1st to 8th grades) as well as secondary schools (9th to 12th grades) within city administrations of Addis Ababa and Dire Dawa

3.3. The regional education bureaus may contextualize without suppressing the purpose for which the code of conduct is issued, or may put into effect this regulation as it is.



# ክፍል ሁለት፡ - የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች

# Part Two: Types of School Related Gender Based Violence

# ክፍል ሁለት፡ - የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች

# Part Two: Types of School Related Gender Based Violence

## 4 ቀላልና ከባድ የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች፣

## 4. Light and Grave forms of School Related Gender Based Violence

በዚህ መመሪያ ክፍል አንድ ተራ ቁጥር 2(1) ለጾታዊ ጥቃት የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የጾታዊ ጥቃት ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል ፣

The definitions listed under number 2 of this code of conduct are applicable while acts of SRGBV include the following;

### 4.1 ቀላል የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች ፣

### 4.1. Less Severe forms of School Related Gender Based Violence

4.1.1 አስነዋሪ በሆነ መልኩ ወሲብ ቀስቃሽ የሰዉነት ክፍሎችን/አካላትን አጋልጦ ማሳየትና ለወሲብ በሚያነሳሳ መልኩ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ ፣

4.1.1. Exposing sexual/body parts and showing movements/ dancing in a way that is sexually provocative,

4.1.2 ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ከትምህርት ቤቱ ደንብና መመሪያ ዉጪ የደንብ ልብስን (ጋወን ወይም ዩኒፎርምና ቱታ) ባለማድረግ ወይም በአግባቡ ባለመጠቀም ለወሲብ ስሜት በሚያነሳሳ ሁኔታ አካልን አጋልጦ ማሳየት ፣እንዲሁም የደንብ ልብስ የሌላቸዉ ሰራተኞች አካላቸዉን ለወሲብ ስሜት በሚያነሳሳ መልኩ አጋልጦ መልበስ ፣

4.1.2. Revealing the body in an immodest way that is sexually provocative in school hours against the regulations and Code of Conducts of the school by not wearing uniforms (for the school community that has uniforms like teachers and students) or dressing up in a way that provokes others sexually (for the school community that does not have uniforms)

4.1.3 ጾታን የሚያንቋሽሹ ፅሁፎችን ፣መጽሔቶችንና ምስሎችን ወደ ትምህርት ቤት ይዞ መምጣት ፣ ለሌሎች ማሳየት እንዲሁም መለጠፍ ፣

4.1.4. ጾታን ማንቋሸሽ ፣ ማጥላላት ፣ ማናናቅና ፣ ወሲባዊ ሁኔታን የሚያንፀባርቁ ቀልዶች ፣ ቧልቶች ፣ አስተያየቶች ፣ ጥያቄዎች ፣ ገጠመኞች እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከሌላው ሰው ፈቃድ ውጪ መናገርና ማስተላለፍ ፣

4.1.5.የአንድ ሰው ፆታ ወይም ተክለ ሰውነት ወይም አለባበስን በተመለከተ አሉታዊ አስተያየቶች ፣ ነቀፌታዎች ፣ ያልተፈለጉና አዋራጅ መገለጫዎችን ፣ ቁጣ ቀስቃሽ ቅፅል ስሞችን መጠቀም ፣

4.1.6 የወሲብ ምስልን ፣ ጾታን የሚያንቋሽሹ ፎቶግራፎችና ምስሎችን እና የፅሁፍ መልእክቶችን በ ኤ ሌ ክ ት ሮ ኒ ክ ስ መሣሪያዎች ማለትም በሞባይል ፣በኮምፒዩተርና በድረ ገጽ በመሳሰሉት ለመመልከትና ለመቀበል በግልጽ ፍቃደኝነቱን ላልገለጸ ሰው ማሳየት ወይም ማስተላለፍ ፣

4.1.3. Bringing to school, showing or posting writings, magazines or pictures that discriminate a specific gender,

4.1.4. Gender discrimination, blackmailing, belittling, telling and communicating erotic jokes, comments, questions, encounters or other similar activities done against the will of the other,

4.1.5. Using negative comments, discriminations, name calling, belittling explanations while talking/ speaking about a person’s gender, physique or way of dressing

4.1.6. Showing or passing sexually provocative pictures, gender discriminating pictures and photographs and text messages via electronic devices such as mobile phones, computers and websites for a person who has not openly expressed willingness to watch or receive them,

4.1.7 የተግባር ትምህርቶችን (የሰዉነት ማጎልመሻና የቤተ ሙከራ ትምህርት) በሚሰጥበት ወቅት ሆን ብሎ ወሲባዊ ትንኮሳን በሚያመላክት መልኩ የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ፣

4.1.8 በስራ ልብስ (ጋወን ወይም ቱታ) ፣በቤተ ሙከራ ፣ በትምህርትና ስልጠና ክፍል ግድግዳዎች ፣ ሽንት ቤቶች ፣ የማደሪያ ክፍሎች እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ሌሎች ቦታዎች ውስጥ ወሲብ ቀስቃሽና ጾታን የሚያንቋሽሹ ስዕሎችን መሳልና ጽሑፎች መፃፍ ፣

4.1.9 ወሲብ ቀስቃሽ ንቅሳቶችን ለእይታ ግልጽ በሆነ መልኩ በሰዉነት አካል ላይ በመነቀስ በትምህርት ቤቱ ዉስጥ መታየት ፣

## 4.2 ከባድ የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች ፣

4.2.1 የወሲብ ምስልን ፣ ፎቶግራፎች እና የፅሁፍ መልእክቶችን በህትመት ውጤቶች እንዲሁም በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ማለትም በሞባይል ፣በኮምፒዩተርና በድረ ገጽ በመሳሰሉት ማሳየት ወይም ማስተላለፍ ፣

4.1.7. Deliberate showing of body gestures/movements that imply sexual harassment during practical academic sessions (physical education or laboratory sessions),

4.1.8. Drawing pictures or writing texts that are sexually provocative in nature or devaluate a specific gender on work uniforms, walls of laboratories, class and training rooms, toilets, dormitories as well as other areas of the school,

4.1.9. Wearing tattoos that are sexually provocative in a way that they are revealed to others while in the school compound,

## 4.2. Grave forms of Gender Based Violence

4.2.1. Showing or passing erotic/pornographic pictures, photos or texts that are in print or digitalized (on mobile phones, computers and websites)

4.2.2 በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች (የተንቀሳቃሽ ስልኮች ፣ኮምፒዩተር) በትምህርት ቤቱ ሚኒ ሚዲያ ፣ በድረ ገፅ ወይም በሌሎች መሰል መንገዶች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባልን ፣ቤተሰብንና ዘመድን ምስል በመጠቀም ወይም በማስመሰል ወሲባዊ ስብእናን የሚያጋልጡና ጾታን የሚያንቋሽሹ መልእክቶችን ማስተላለፍ

4.2.3. የሌሎችን አካላት ለወሲብ በሚገፋፋ መልኩ በመዳሰስ ፣ በመተሻሸት ፣በመሳም የሰውነት ንክኪ መፍጠር

4.2.4 አንድን የትምህርት ማህበረሰብ አባል ለወሲብ ተግባር ለማሰማራት ማግባባት ወይም ማሰማራት

4.2.5 ከአንድ ግለሰብ የወሲብ ጥቅም ለማግኘት የፈተናና የተከታታይ ምዘና ጥያቄን ፣መልስንና ዉጤት መስጠት ወይም ገንዘብን ፣ መጠለያን ፣ ምግብንና ሌሎች ቁሳቁሶችን መደለያ በማድረግ ወሲብ ለመፈፀም መሞከር ወይም መፈጸም

4.2.2. Communicating messages that reveal sexual personality or devaluate gender using electronic devices (mobile phones, computers), school mini-media, web-pages or other similar methods and making use of pictures or imitations of any member of the school community, families and relatives for such purposes

4.2.3. Making physical contact, caressing, petting or kissing the bodies of others in a way for sexual initiation

4.2.4. Persuading or involving any member of the school community for sexual activities

4.2.5. Making use of learning assessment grading or marking for the sake of sexual exploitation or persuading with the use of money, shelter, food or other necessities in an attempt to have sex with the other person or actually engaging in sexual activity

4.2.6 ከአንድ ግለሰብ ለቀረበ የወሲብ ጥያቄ የተሰጠ አሉታዊ ምላሽን መሰረት በማድረግ የተከታታይ ምዘናና የፈተና ዉጤት መቀነስ መሰረዝ እና ሌሎች አሉታዊ ጫናዎችን ማሳደር

4.2.7 የአንድን የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል በትምህርት ቤት ዉስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ዉጪ ጾታን መሰረት በማድረግ በነፃነት የመንቀሳቀስ መብትን በመጋፋት እና በመከታተል የስነልቦና ጫና ማሳደር ፣ያለ በቂ ምክንያት ከስልጠናና ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት ፣

4.2.8 የስራ አፈጻጸም ግምገማ ፣ ለስልጠና ውጤት ፣ ለደረጃ እድገት ፣ የትምህርትና ስልጠና እድልና ዝዉዉር ለመስጠት ወሲባዊ ግንኙነትን እንደ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ፣

4.2.9 ከአንድ ግለሰብ ለቀረበ የወሲብ ጥያቄ የተሰጠ አሉታዊ ምላሽን መሰረት በማድረግ የስራ አፈጻጸም ግምገማ ፣ የስልጠና ውጤት ፣የደረጃ እድገት ፣ የትምህርትና ስልጠና እድልና ዝዉዉር መከልከል እና ሌሎች አሉታዊ ጫናዎችን ማሳደር።

4.2.6. Jeopardizing test and learning assessment grades such as giving incomplete results or imposing negative influences based on denial of sexual advances or rejection of initiation for sexual activity

4.2.7. Denying freedom of movement or following up and tagging along in a way that results in psychological influence on any member of the school community based on gender whether inside or outside the school compound, dismissing from class or training rooms without adequate and appropriate reason,

4.2.8. Putting sexual relationship as a pre-requisite for recognizing or grading as good performance, results of trainings, job promotions, opportunities for further academia and trainings and imposing other negative influences,

4.2.9. Denying appropriate performance evaluation results, results of trainings, job promotions, opportunities for further academia and trainings and imposing other negative influences based on a person's rejection of request for sexual intimacy

4.2.10 የወሲብ ጥያቄ በቀረበለትና ጾታዊ ጥቃት በደረሰበት ግለሰብ ዙሪያ ባሉ ሶስተኛ ወገኖች ላይ ጫና ማሳደር።

4.2.11 የወሲብ ተግባርን ለመፈጸም በማሰብ የትምህርት መሣሪያዎችና ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች መቀማት ፣ መደበቅና መያዝ ማድረግ ፣

4.2.12 በቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ላይ በመምህራን ፣ በአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና ርእሳነ መምህራን የሚፈጸም ማንኛዉም አይነት ጾታዊ ጥቃት ፣

4.2.13 ጾታን መሰረት ያደረገ አድልዎን መፈፀም ፣

4.2.14 በትምህርት ቤቱ ዉስጥ ወሲብ መፈጸም ፣

4.2.15 የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ወይም አስገድዶ መድፈር ፣

4.2.16 ቀላል ጾታዊ ጥቃትን በመፈፀም በተወሰደበት የቅጣት እርምጃ ባለመታረም በተደጋጋሚ ቀላል የጾታዊ ጥቃት መፈፀም ፣

4.2.10. Imposing negative influences on third parties that are related to the person who was asked for sexual intimacy or a person who is a victim of gender based violence

4.2.11. Robbing, hiding, or snatching academic materials or valuables as a means of persuading in the intention of obtaining sexual gratification,

4.2.12. Any form of gender based violence committed on pre-school, primary school or secondary school students by teachers, administration, deputy directors or support staff

4.2.13.Committing gender based favor,

4.2.14. Having sexual intimacy inside the school,

4.2.15. Attempt of rape or committing rape

4.2.16. Not learning from previous disciplines for Common forms of gender based violence and committing them repeatedly,

4.2.17 በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸም ቀላል የጾታዊ ጥቃት በከባድ የጾታዊ ጥቃት አይነቶች ከተመለከቱት የጥፋት ድርጊቶች ጋር እኩል ክብደት ይኖራቸዋል ፡፡

4.2.18 በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ቀላልና ከባድ የጾታዊ ጥቃት አይነቶች እንዲፈጸም የተባበረ ወይም ያመቻቸ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል እንደጥፋቱ ድርጊት በዚህ መመሪያ ክፍል ሶስት ተራ ቁጥር 5 የተመለከተው የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል ፡፡

4.2.17. Any Common forms of gender based violence that are committed against persons with disability are considered as a Grave form of gender based violence,

4.2.18. Any member of the school community who cooperated or participated in committing any of the Common or Grave forms of violence listed in this code of conduct will be subjected to punishment which is explained in number 5 of the third part of this code of conduct



# ክፍል ሶስት
# የሚወሰዱ የእርምጃ ዓይነቶች

# Part Three: Types of Punishments

ክፍል ሶስት፡ -
የሚወሰዱ የቅርምጃ ዓይነቶች

# Part Three: Types of Punishments

## 5. የሚወሰዱ የቅርምጃ ዓይነቶች፣

ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 4 የተመለከቱትን የጾታዊ ጥቃት አይነቶች ከፈጸመ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆነው እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት የእርምጃ አይነቶች አንዱ ተፈጻሚ ይደረግበታል ፡፡

### 5.1. በተማሪ ላይ የሚወሰድ ቀላል እርምጃ ፣

ሀ. በቃለ ጉባኤ የተደገፈ ተግሳፅ/የቃል ማስጠንቀቂያ ፣

ለ.የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ፣

### 5.2. በተማሪ ላይ የሚወሰድ ከባድ እርምጃ ፣

ሀ. ለአንድ የትምህርት ዓመት ማገድ እና ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እንዳይዛወር መሸኛ መከልከል ፣

## 5. Types of Punishments

If any member of the school community commits any one of the gender based violence listed under number 4 of part two of this regulation, the following punishments are applicable in addition to the punishments stipulated in other parts of the law with the punishment determined according to the severity of the violence.

### 5.1. Light form of Punishment applicable on a student

a) Oral warning which is put on recording in writing

b) Written warning

### 5.2. Severe form of Punishment applicable on student

a) suspension from education for a year and denying a formal withdrawal to prohibit transfer to another school

ለ. ለሶስት የትምህርት ዓመት ማገድ እና ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እንዳይዛወር መሸኛ መከልከል ፣

ሐ.በትምህርት ዘመኑ ትምህርቱን አጠናቆ ለብሄራዊ ፈተና (8ኛ ፣10ኛ ፣12ኛ) የሚዘጋጅ ከሆነ ፈተናዉን እንዳይወስድ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከአንድ እስከ ሁለት አመት ማገድ ፤ ወይም ብሄራዊ ፈተና ከወሰደ በኋላ ጥፋት የፈጸመ ከሆነ የፈተና የምስክር ወረቀትና መሸኛ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከአንድ እስከ ሁለት አመት እንዳይሰጠዉ ማድረግ ፣

መ. በሀገሪቱ በየትኛውም ትምህርት ቤት ለአምስት ዓመት እንዳይማር ማገድ ፣

## 5.3. በመምህራን እና አስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ላይ የሚወሰድ ቀላል እርምጃ ፣

ሀ. በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የቃል ማስጠንቀቂያ ፣

ለ. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ፣

ሐ. እስከ 1 ወር የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት ፣

## 5.4.በመምህራን እና የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ላይ የሚወሰድ ከባድ እርምጃ ፣

b) suspension from education for three years and denying a formal withdrawal to prohibit transfer to another school

c) If s/he is sitting for national exam (8th, 10th or 12th grader) prohibiting from attending the exam for a year or two depending on the severity of the violence, if the violence is committed after sitting for national exams denying certificates and clearance for a year or two depending on the severity of the violence

d) Prohibiting from attending in any of the schools in the country for 5 years

## 5.3. Light form of Punishment applicable on teachers, school administration and support staff

a) Oral warning put on recording in a written form

b) Written warning

c) salary up to 1 month

## 5.4. Severe form of Punishment applicable on teachers, school administration and support staff

ሀ. የሦስት ወር ደመወዝ መቀጮ ፤

ለ. ካለበት የደመወዝ ደረጃ እስከ ሁለት ደረጃ ዝቅ ማድረግ ፤ ጀማሪ ከሆነ ለአንድ ጊዜ ባለበት ደረጃ ማቆየት ፤

ሐ. የሙያ ፍቃዱን ለሁለት አመት ማገድ እና ሌላ ቦታ ሄዶ በተመሳሳይ ሙያ ለሁለት ዓመት እዳይቀጠር ሰርኩላር ማስተላለፍ ፤

መ.ከሥራ ማሰናበትና ሌላ ቦታ ሄዶ በተመሳሳይ ሙያ እዳይቀጠር ሰርኩላር ማስተላለፍ ፤

## 5.5 በርዕሰ መምህር ላይ የሚወሰድ ቀላል እርምጃ

ሀ. የሦስት ወር ደመወዝ መቀጮ ፤

ለ. ካለበት የደመወዝ ደረጃ እስከ ሁለት ደረጃ ዝቅ ማድረግ ፤ ጀማሪ ከሆነ ለአንድ ጊዜ ባለበት ደረጃ ማቋየት

ሐ. ከሥልጣን ማሰናበት ፤

## 5.6. በርእሰ መምህር ላይ የሚወሰድ ከባድ እርምጃ

ሀ.የቅጣት ዉሳኔዉ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ለሶስት ዓመት ከስራ ማገድና እና በተመሳሳይ ሙያ ለሶስት ዓመት

a) penalty salary of 3 months

b) demotion of job position in two ranks, if it's a junior, keeping them at the same post up to a certain time

c) Banning the work license for two years and passing a circular letter to prevent from working in other schools

d) Dismissing from work and passing a circular letter to prevent from being hired for a similar work

## 5.5. Light form of Punishment applicable on the school Principal

a) Penalty of 3 months' salary

b) Lowering the salary to two scales, if it's a junior keeping the scale the same for a certain period of time

c) Dismissal from work

## 5.6. Severe form of Punishment

applicable the school Principal

a) suspension from work for three years starting from the date the decision of punishment is rendered and passing a circular letter that

ሌላ ቦታ ሄዶ እናዳይቀጠር ሰርኩላር ማስተላለፍ ፣

suspends the principal for three years from being hired for the same post in other schools

ለ.የሙያ ፈቃዱን ለአምስት አመት ማገድ

b) Suspending the Job permit for five years

ሐ. ከስራ ማሰናበትና ሌላ ቦታ ሄዶ በተመሳሳይ ሙያና ሃላፊነት እንዳይቀጠር ወይም እንዳይመደብ ሰርኩላር ማስተላለፍ ፣

c) Dismissal from work, passing circular letter to prohibit from working at a similar post or responsibility



## ክፍል ኣራት፡ - የጾታዊ ጥቃት ኣቤቱታ ኣጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ ኣቅራቢ ኮሚቴን በተመለከተ

## Part Four: Concerning School Related Gender Based Violence Complaint Investigation and decisions recommending committee

## ክፍል አራት፡- የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴን በተመለከተ

## Part Four: Concerning School Related Gender Based Violence Complaint Investigation and decisions recommending committee

### 6. የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና ዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ አወቃቀር፣

6.1. የጾታዊ ጥቃት አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ 7 አባላት የሚኖሩት ሲሆን አወቃቀር የፆታ ስብጥርን ያማከለ መሆን አለበት።

6.2. የጾታዊ ጥቃት አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ናቸዉ ፣

ሀ. የትምህርት ቤቱ የስርዓተ-ፆታ ክበብ ተጠሪ ተማሪ ፣

ለ. በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የሚመረጥ አንድ ተወካይ ተማሪ

ሐ. የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (ወተመህ) ሰብሳቢ

መ. የትምህርት ቤቱ መሰረታዊ የመምህራን ማህበር ሰብሳቢ ፣

ሠ. ከአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሚመረጥ አንድ ተወካይ ፣

### 6. Organization of the School Related Gender Based Violence Complaint Investigation and decisions recommending committee

6.1. The School Related Gender Based Violence Complaint Investigation and decisions recommending committee has 7 members constituted of both sexes

6.2. The following are the members of School Related Gender Based Violence Complaint Investigation and decisions recommending committee

a) A student who is the school’s Gender Club representative

b) A representative who is elected by the students

c) Chairperson of the Parent Teacher Student Association

d) Chairperson of the school’s Teachers’ Association

e) A representative elected by the

ረ. የትምህርት ቤቱ መሰረታዊ መምህራን ማህበር ስርአተ ጾታ ተጠሪ እና

ሰ.የትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ምክትል ርእሰ መምህር የኮሚቴው አባልና ጸሃፊ

6.3. ቅድመ መደበኛና የአንደኛ ደረጃን (ከ1ኛ-4ኛ) በተመለከተ ከላይ በ6.2. በሀ እና ለ የተጠቀሱት አባላት የኮሚቴው አባል ስለማይሆኑ ጉዳዩ በተቀሩት የኮሚቴዉ አባላት ይታያል

6.4 የትምህርት ቤቱ መሰረታዊ መምህራን ማህበር ስርአተ ጾታ ተጠሪ የኮሚቴው ሰብሳቢ ትሆናለች

6.5 የኮሚቴዉ ምክትል ሰብሳቢ በኮሚቴዉ አባላት የሚመረጥ ይሆናል ፣

6.6 የኮሚቴ የስራ ዘመን 2 ዓመት ሆኖ የተሻለ ስራ የሰሩት የኮሚቴዉ አባላት በድጋሚ ለአንድ ጊዜ መመረጥ ይችላሉ

administration and support staff

f) A gender representative for the school's Teachers Association and

g) The school's teaching-learning process vice principal as a committee member and secretary

6.3. Since the members listed under 6.2. a and b cannot be members at pre-school and primary school (1st grade – 4th grade) levels, the issue is to be investigated by the rest of the committee members

6.4. The gender representative for the school's Teachers Association becomes the chairperson for the committee

6.5. The deputy chairperson of the committee is elected by the members of the committee

6.6. The term of service of the committee is two years while the members of the committee who are known for better accomplishments could be elected to serve for one more additional term

## 7. የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና ዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ አባላት መምረጫ መስፈርት፣

ማንኛውም የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና ዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ አባል ፣

7.1. በመልካም ስነ-ምግባር አርአያ የሆነ ፣

7.2. ከዚህ ቀደም በጾታዊ ጥቃት ወይም በሌሎች ወንጀሎች ተከሶ ያልተቀጣ ፣

7.3. ቢያንስ በትምህርት ቤት ውስጥ ለአንድ ዓመት የቆየ መሆን አለበት ፡፡

## 8. የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣

8.1. መመሪያዉን ለተቋሙ ማህበረሰብ የማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን ይሰራል ፡፡

8.2. የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴ በአንቀጽ 11.3 የተጠቀሱትን ዝርዝሮች የያዘ የአቤቱታ

## 7. Criteria for choosing members SRGBV Complaint Investigation and decisions recommending committee

Any one of the members of SRGBV Complaint Investigation and decisions providing committee should be:

7.1. Exemplary in good discipline

7.2. Never been accused and punished for gender based violence or other crimes

7.3. Have been in the school for at least a year

## 8. The Authority and job descriptions of the SRGBV Complaint Investigation and decisions providing committee

8.1. Introducing the code of conduct and creating awareness to the community of the institution

8.2. The SRGBV Complaint Investigation and decisions providing committee prepares forms that contain the lists under

ማመልከቻዎች የሚቀርቡባቸው ቅጾች ማዘጋጀት አለበት ፡፡

8.3. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የጾታዊ ጥቃት ጥፋት ድርጊት ተፈጽሞብኛል የሚል አቤቱታ ሲቀርብለት በመመርመር የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

8.4 አቤቱታዎችን ሲመረምር አቤቱታ አቅራቢን ፣አቤቱታ የቀረበበትን ወይም ምስክሮችን የመጥራትና የመስማት ፣ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች (የጽሁፍና የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃዎችን) እንዲቀርቡለት የማዘዝ ፣ ሰነዱ ባለበት ቦታ ሄዶ የማየትና ሌሎች ለምርመራ ተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል ፡፡

8.5. በርእሰ መምህር ወይም በምክትል ርእሳነ መምህራን የጾታዊ ጥቃት ተፈጽሞብኛል የሚል አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ ኮሚቴው ጉዳዩን አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ በየደረጃዉ ስልጣን ላለው የትምህርት መዋቅር ያቀርባል ፡፡

8.6 ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ ከቀጠሮዉ 10 ቀናት

11.3 which can be used for filing complaints

8.3. When complaint informing that gender based violence has occurred in the school and is received, the committee investigates and provides decisions

8.4. Whenever complaints are investigated, the committee calls for the person who filed the complaint, the person who is accused of violence or witnesses to listen to the testimony; requests for documents (be it written or digital evidences) that are related to the matter under investigation, be present physically to look through the documents if they are not presented to them and performs other activities necessary for the investigation.

8.5. Whenever complaints of school related gender based violence are received against the school director or deputy director, the committee investigates the matter and passes the decisions to the next upper hierarchy in the education structure for its decision.

8.6. The committee should inform the person who is accused

አስቀድሞ አቤቱታ ለቀረበበት ሰው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት ፡፡

8.7 በአቤቱታዎች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከመቅረቡ በፊት ጾታዊ ጥቃቱ እንዲቆም የሚያደርግ ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል ፡፡

## 9. የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

9.1. ኮሚቴው በ15 ቀን አንድ ጊዜ ወይም ለትምህርት ቤቱ የጾታዊ ጥቃት አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ሰብሳቢ/ጸሃፊ በቀረቡ አቤቱታዎች አስቸኳይነት መሠረት በማድረግ ሊሰበሰብ ይችላል ፡፡

9.2. ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሣኔ ሃሣብ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል ፤ድምፅ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል ፡፡

9.3. የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለዉ የኮሚቴዉ ከግማሽ በላይ አባላት ሲገኙ ነው ፡፡

9.4 የጾታዊ ጥቃት አቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴው ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢዉ ተክቶ ይሰራል ፡፡

of violence 10 days prior to the appointment.

8.7. The committee passes temporary orders that prevent the gender based violence from happening before decisions are provided on the complaints of violence

## 9. Meetings

9.1. The committee holds meetings once in 15 days and also when complaints of violence are received by the SRGBV Complaint Investigation and decisions providing committee

9.2. The decision provided by the committee passes when voted by the majority. If equal numbers of the committee are for it and against it, decision is passed based on which decision the Chair person has voted for,

9.3. The committee is said to be able to undergo a meeting when more than half of the members are present

9.4. Whenever complaints are received in the absence of the chair person for the committee the vice-chair leads the meetings

## 10. የኮሚቴ አባላት መከተል ስለሚገባቸው የሥነ-ምግባር መርሆዎች፣

10.1. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በኮሚቴ አባልነቱ ያወቃቸውን ማንኛውንም ጉዳዮች በሚስጥር መጠበቅ አለበት ፡፡

10.2. ማንኛውም የኮሚቴ አባል ለውሣኔ የቀረቡ አቤቱታዎች ከራሱ ፣ ከቅርብ ጓደኛው ወይም ከዘመዱ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ ከአባልነት እራሱን ማግለል አለበት ወይም ይህንን አስመልክቶ ምስክር ፤ መረጃና ማስረጃ ከቀረበበት የቀረበዉን አቤቱታ እንዳያይ ይደረጋል ፡፡

10.3. ማንኛውም የኮሚቴ አባል አቤቱታዎችን በሚያይበት ወቅት በፆታ ፣ በዘር ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ አመለካከት ፣ በአካል ጉዳት ወይም ሌላ ሁኔታን መሠረት ያደረገ አድልዖ መፈፀም የለበትም ፡፡

10.4. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች በኮሚቴው የሚወሰኑ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የጣሰ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚቴውን ሥራ ያደናቀፈ

## 10. Principles of discipline followed by the Committee Members

10.1. Confidentiality should be maintained concerning any complaints and issues handled by the committee

10.2. Any member of the committee should not take part in the investigation and decision making of complaint when the complaint is related to her/himself, a close friend or relative or will not be allowed to take part when witnesses, information or evidence is presented about it.

10.3. Any member of the committee should not favor based on gender, race, religion, political stands, disability or any other reason while working on complaint reports

10.4. Any member of the committee who conducts against the principles listed above or hindered the work of the committee in anyway is removed from

የኮሚቴ አባል ከአባልነቱ መሠረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በትምህርት ቤቱ ደንብ መሰረት በዲስፕሊን ጉድለት ተጠያቂ ይሆናል ፡፡

## 11. የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት፣

11.1. ማንኛውም ቀላል የጾታዊ ጥቃት ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው ወይም የተጠቂዉ ወላጅና አሳዳጊ ወይም ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል አካል ጥቃቱ ከተፈጸመበት ወይም መፈጸሙ ከታወቀት ጊዜ ጀምሮ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለኮሚቴዉ ሰብሳቢ ወይም ጸሃፊ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡

11.3. ማንኛውም ከባድ የጾታዊ ጥቃት ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው ወይም የተጠቂዉ ወላጅና አሳዳጊ ወይም ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል አካል ጥቃቱ ከተፈጸመበት ወይም መፈጸሙ ከታወቀት ጊዜ ጀምሮ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ለኮሚቴዉ ሰብሳቢ ወይም ጸሃፊ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል ፡፡

11.3. በዚህ አንቀጽ ቁጥር 11.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው በተጠቀሰው

membership in the committee while the lack of discipline is to be dealt with according to the school's disciplinary measure.

## 11. Formalities to be fulfilled while making a Complaint

11.1. Anyone who complains that a less severe form of SRGBV has been committed on her/him, family memeber or care giver or any party whom the issue concerns should report within the next 10 working days since the violence was committed or was known to be committed in written form to the chair person or the secretary of the committee

11.2. Anyone who complains that a severe form of SRGBV has been committed on her/him, family or care giver or any party whom the issue concerns, it should be reported within the next 30 working days since the violence was committed or was known to be committed in written form to the chairs person or the secretary of the committee

11.3. While 11.1 of the code of conduct is applicable if the person reporting the violence explains that

ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜው የሚቆጠረው ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል ፡፡

11.4. በአቤቱታ ማመልከቻ ውስጥ መካተት ስለሚገባቸው ዝርዝሮች ማንኛውም የአቤቱታ ማመልከቻ ፡-

ሀ. የአቤቱታ አቅራቢው ስም ከነ አያት

ለ. የሚማርበት ክፍል ፣ የሚያስተምርበት የትምህርት ክፍል ወይም የሚሰራበት የስራ ክፍል

ሐ. ድርጊቱ የተፈፀመበት ቀን ፣ ቦታና ጊዜ

መ. ተፈፀመ የተባለው የጾታዊ ጥቃት ዓይነት/የድርጊቱ መገለጫዎች

ሠ. የሚታወቅ ከሆነ የጥቃቱ ፈፃሚ ስምና የመማሪያ ክፍል ፣ የትምህርት ክፍል ወይም የሥራ ክፍል ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መለያ

ረ. ምስክር ካለ የምስክሩ ስም እና አድራሻ

s/he could not report in the dates specified due to impossibilities the reporting time begins from the day where the reasons for impossibilities is solved or is no more hindrance to report the violence

11.4. Details to be included in the Report of Complaint

Every report of complaint should include the following:

a) Full name of the person reporting the complaint

b) The classroom s/he attends in, the department s/he teaches in or the department s/he works in

c) The date, place and time of the committed violence

d) The type of the school related gender based violence/ expressions of the act

e) The name, classroom, teaching or work department or any form of identification of the person who is accused of committing the violence (if known)

f) The name and address of the witness (if there is/are witness/es)

ሰ. በአቤቱታ አቅራቢ እጅ የሚገኙ የጽሁፍም ሆነ ሌሎች ማስረጃዎች ወይም በእጅ የማይገኙ ከሆኑ የሚገኙበትን ቦታ

ቀ. የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማና አቤቱታ የቀረበበትን ቀን መያዝ ይኖርበታል ፡፡

## 12. ጥበቃ ከሚያስፈልገዉ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት ስለሚደረግ ተገቢ ጥበቃ

ሀ. ጥበቃ የሚያስፈልገው ተማሪ በሆነበት ጊዜ ተማሪዉ የሚማርበት ክፍል እንዲለወጥለት ወይም ፈተናውና ተከታታይ ምዘናዉ በሌላ አራሚ እንዲታረምለት እና እንዲታይለት ማድረግ ፣

ለ. ጥበቃ የሚያስፈልገው መምህር ወይም አስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ከሆነ በፍቃደኝነት ወደ ሌላ የስራ ክፍል ወይም የስራ ቦታ እንዲዛወር ወይም አቤቱታ የቀረበበት ሰዉ ምንም አይነት ጥቃት እንዳያደርስ የግዴታ ሰነድ ማስፈረምና ተገቢነት ያለው ጥበቃ ማድረግ ፡፡

ሐ. ጥበቃ የሚያስፈልገው ርእሰ መምህሩ ከሆነ አቤቱታ የቀረበበት ሰዉ ምንም አይነት ጥቃት እንዳያደርስ የግዴታ ሰነድ ማስፈረምና ተገቢነት ያለው ጥበቃ ማድረግ ፡፡

g) Written or other forms of evidence that are in the hands of the person who reports the complaint or if they are not available with the person who reports the complaint, the place where they are found

h) The signature of the person who reported the complaint and the date when the report is submitted to the committee

## 12. Legitimate Protection for the member/s of the School Community who needs Protection

a) When it is a student that needs protection, safeguard her/his classroom attendance and ensure legitimate learning assessment results

b) When a teacher, administration staff or support staff needs protection, ensure her/his safety, or secure a signature of restraint form any attempt to harm the compliant

c) When the school principal needs legitimate protection make the person who is accused of committing the violence sign commitment of restraint from any harm

## 13. ጸቤቱታ ማቅረብ ስለማይቻልባቸው ሁኔታዎች

13.1. በዚህ መመሪያ ቁጥር 11.1 እና 11.2 የተጠቀሰው የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነና በማንኛውም ሁኔታ ጾታዊ ጥቃት ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ አንድ አመት ያለፈው እንደሆነ።

13.2 ቀደም ሲል ጉዳዩ በአቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ታይቶ በየደረጃዉ ስልጣን ያለዉ የትምህርት መዋቅር የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ ፡ ፡

## 14. ጸቤቱታ የቀረበበት ሰው የመደመጥ መብት

ማንኛውም በጾታዊ ጥቃት ተግባር አቤቱታ የቀረበበት ሰው የቀረበበትን አቤቱታ የማወቅ ፣ ራሱን የመከላከልና የመደመጥ መብቱ የተጠበቀ ነው ፡ ፡

## 15. የዉሳኔ ሃሳብ ጸቀራረብና የዉሳኔ ጸሰጣጥ ስነስርዓት፣

15.1 የአቤቱታ አጣሪና የዉሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት የጾታዊ ጥቃት ድርጊት ተፈጽሞብኛል የሚል

## 13. Conditions where Complaints are not to be Reported

13.1. If the time limited specified in 11.1 and 11.2 has passed and if in any way one year has passed since the SRGBV has been committed

13.2. If the issue has already been investigated by the committee and the final decision has been made by the appropriate authority in the academic structure

## 14. The right of the accused

Anyone who is accused of committing gender based violence has the right to know the complaints reported against them, defend themselves and to be listened to of any possible explanations.

## 15. Formalities of recommending and making decisions

15.1. SRGBV Complaint Investigation and decisions providing committee investigates the complaint in not more than

አቤቱታ ሲቀርብለት በመመርመር ከ30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ለርእሰ መምህሩ በጹሁፍ የዉሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

15.2 የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር በኮሚቴዉ የዉሳኔ ሃሳብ ከቀረበለት ቀን ጀምሮ ከ5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን አጣርቶ በጹሁፍ ውሣኔ ይሰጣል ፡፡

15.3 የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር የጾታዊ ጥቃት ፈፅሞብኛል የሚል አቤቱታ ለኮሚቴዉ ሲቀርብ አቤቱታውን በመመርመር ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ የውሳኔ ሃሳብ ለወረዳዉ ትምህርት ጽህፈት ቤት ያቀርባል።

15.4 በየደረጃዉ ያለዉ የትምህርት መዋቅር የዉሳኔ ሃሳብ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን አጣርቶ በጹሁፍ ውሣኔ ይሰጣል ፡፡

15.5 በዉሳኔ ሰጪ አካላት የተሰጡ ዉሳኔዎች ለባለጉዳዩና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ አለበት።

15.6 በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ ማናቸውም ዓይነት ውሣኔዎች አቤቱታ አቅራቢውንና አቤቱታ የቀረበበትን የትምህርት

30 days and provides decision in writing to the school director.

15.2. The school director clarifies the issue in not more than 5 days since the reception of the proposed decision by the committee and endorses the decision in writing.

15.3. When complaints are reported of the school director committing gender based violence the committee investigates the issue in not more than 15 days and passes the proposed decisions to the Woreda's education bureau.

15.4. The respective academic structure investigates the issue in not more than 30 days after the reception of the provided decisions by the committee and makes final verdict.

15.5. The decisions made should be announced for the person who has reported the complaint as well as to the school community.

15.6. Any verdict passed according to this code of conduct would not hold the person reporting the complaint or the member of school community accused for

ማህበረሰብ አባል ጉዳዩ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ መደበኛ የፍርድ ሂደቶችን እንዳይከተል አያግዱትም ፡፡

violence from presenting the case to court to be dealt with according to other national or regional laws.

## 16. ይግባኝ

## 16. Appeal

16.1 በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ አካል ዉሳኔዉን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ይግባኙን በየደረጃዉ ስልጣን ያለዉ የትምህርት መዋቅር ማቅረብ አለበት ፡፡

16.1. Any party that is dissatisfied with the final verdict can appeal to the next ladder in the education hierarchy within 30 working days from the date the decision is announced.

16.2 በየደረጃዉ ስልጣን ያለዉ የትምህርት መዋቅር ጉዳዩ በይግባኝ ሲቀርብለት እስከ አንድ ወር ባለዉ ጊዜ ውስጥ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አለበት ፡፡

16.2. The respective body in the academic structure should investigate appeals and pass a decision within not more than a month.

## 17. የቅጣት ሪኮርድ መቆያ ጊዜ

## 17. The Time Limit of the Punishment Records

17.1. ቀላል የጾታዊ ጥቃት የፈፀመና የተቀጣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል የቅጣት ጊዜ ገደብን ከጨረሰበት ቀን ጀምሮ ለአንድ አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይያዝበታል ፡፡

17.1. Decision passed on less severe form of SRGBV will be documented in perpetrator's personal file for one year.

17.2. ከባድ ጾታዊ ጥቃት የፈፀመና የተቀጣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል የቅጣት ጊዜ ገደብ ከጨረሰበት ቀን ጀምሮ ለሁለት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይያዝበታል ፡፡

17.2. Verdicts made for commitment of severe form of SRGBV will be documented in perpetrator's file for two years after punishment is concluded.




# ክፍል አምስት፡- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

# Part Five: Other Regulations

# ክፍል አምስት፡- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

# Part Five: Other Regulations

## 18. የጾታዊ ጥቃት አጣሪና የውሣኔ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ስለማቋቋም

ማንኛውም ትምህርት ቤት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት መካከል የሚፈፀም ጾታዊ ጥቃትን አጣርቶ የውሣኔ ሃሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ያቋቁማል ፡፡

## 19. ስለ ሌሎች ሦስተኛ ወገኖች

19.1 የተለያዩ ስራዎችን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለመስራት ከሚመለከተዉ የትምህርት መዋቅር ጋር ውል የሚገቡ የስራ ተቋራጮች ፣ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እንዳይተላለፉ በሚገቡት ዉል እንዲካተት መደረግ አለበት ፡፡

19.2 ትምህርት ቤቱ ከሌሎች አካላት ጋር በሚያደርገዉ የዉል ስምምነት መሰረት ተማሪዎች ለተለያዩ ትምህርታዊ ጉብኝቶች ፣ስፖርታዊ ስልጠናዎች ፣ ክበረ

## 18. Establishing Gender Based Violence Complaint Investigation and decisions Recommending committee

Every school establishes a committee that investigates cases of school related gender based violence committed amongst the school community

## 19. Third Party

19.1. The declarations specified in this Code of Conduct should also be observed in case of any work agreement the school has made and engaged any individual or group that may have used accessing the school as an opportunity of committing gender based violence on any of the school community member

19.2. If students tour for academic reasons, sport related activities, festivals and other programs due to the agreements the school has with different

በዓላት እና ለሌሎች ጉዳዮች የሚሄዱ ከሆነ ከላይ በ19.1 የተጠቀሰዉ ተግባራዊ ይሆናል።

## 20. የስርዓተ ፆታ ክበብን በተመለከተ

ማንኛውም ትምህርት ቤት የስርዓተ ጾታ ክበብ ማቋቋምና የክበቡን ተጠሪ መመደብ አለበት ፡፡

## 21. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል የጾታዊ ጥቃት መፈፀሙን ባወቀ ጊዜ ሪፖርት የማድረግ ፣ለምስክርነት ሲጠራ የመቅረብ ፣ በሥራ ኃላፊነቱም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች በእጁ የሚገኙ መረጃዎችና ማስረጃዎችን በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት ፡፡

## 22. ዕርምጃዎችን ተግባራዊ ያለማድረግ

በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጡትን ውሳኔ ሃሳቦች ማንኛውም ትምህርት ቤት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን ተግባራዊ በማያደርጉት ትምህርት ቤቶች ላይ የሚመለከተዉ የመንግስት አካል ተገቢዉን እርምጃ ይወስዳል።

academic institutions it should be conducted according to 19.1 of this Code of Conduct.

## 20. Establishment of Gender Club

For the sake of the implementation of the code of conduct and addressing other gender related issues, every school should establish gender club and assign a representative for it.

## 21. Obligation to Cooperate

Every member of the school community should report, cooperate to testify, pass on any information and evidence that is available at one's disposal related to work responsibilities or other reasons known to her/him. to SRGBV complaint investigation and decision recommending committee.

## 22. Reluctance of any School to Enforce this SRGBV Code of Conduct

Every school has the duty of enforcing the decisions passed according to this code of conduct. The respective government body takes appropriate measures on the schools that do not oblige.

## 23. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ የጾታዊ ጥቃት ክሶች ካሉ ቀደም ሲል በተጀመረበት ሁኔታ ተጣርተው ውሣኔ ያገኛሉ ፡፡

## 24. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም በተቋሙ ዉስጥ ቀደም ብሎ የሚሰራበት መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ አይሆንም ፡፡

## 25. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በትምህርት ሚኒስቴር ከፀደቀበት ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

## 23. Transitional stipulation

Any case of SRGBV that has been investigated before the launching of this code of conduct will be handled according to pervious regulation of the school.

## 24. Inapplicability of the regulation

Any regulation or practice that has been applicable in the institution contrary to this code of conduct is not applicable since the day this code of conduct came in to force

## 25. Entry in to force

This code of conduct is applicable starting from the day it is issued by the Ministry of Education which is 2007 E.C.